# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)

**Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)**


## ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከተባረሩ የኦሮሞ ተማሪዎች ጎን እንቁም !!

ወያኔ በከፍተኛ ፍጥነት ወደ መቃብር ጉድጎድ እየወረደ ባለበት በአሁኑ ወቅት በጣአረ ሞት እንደእብድ ውሻ ከግራና ቀኝ ያገኘውን ሁሉ መናከሱ የሚጠበቅ ነው ። በዚህ የአምባገነኖች ሁሉ መገለጫ በሆነው የመጨረሻ ሰዓት መፈራገጥ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለመመከት ሁሉም የህዝብ ወገን፣ በተለይም ወጣቱ ሐገርና ሕዝብን በማስቀደም የድርጅትን አጥር ጭምር ሰብሮ፣ ዘር፣ ሀይማኖት፣ጾታ፣ወዘተ ሳይገታውና ሳይከፋፍለው በተጠናከረና በተቀናጀ ትግል የዘረኛውን ወያኔ ውድቀት ማረጋገጡ የግድ ነው።

በወያኔ መቃብር ላይም ሕዝብ ወሳኝ የሚሆንበት፣ ሰባዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባት የሕግ የበላይነት የሰፈነባትና ሕዝብ የስልጣን ባለቤት የሚሆንባትን እትዮጵያን  ለመገንባት የወጣቱ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ኢሕአፓ ወክንድ ያምናል።

ይህንንም እውን ለማድረግ ሁሉም ወጣት ክንዱን አስተባብሮ የሚሰነዘርበትን ጥቃት በጋራ መመከት አማራጭ የማይገኝለት የታሪክ ግዴታ ነው። ኢሕአፓ ወክንድ የወያኔን ወያኔነት በሚገባ የተገነዘበና በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ የሕብረተሰባችን ክፍሎች ላይ የሚፈጽመው ግፍና ጥቃት ወያኔ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ካለው አኩይ ራእይ የሚመነጭ ለመሆኑ ቅንጣትም ብዥታ የለውም።

በመሆኑም ወያኔ ባሰማራቸው እርጉም መልእክተኞቹና አባሎቹ አማካኝነት በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ውስጥ ባሉ የትግራይና የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች መሃከል ግጭት እንዲፈጠር ካደረገ በኋላ ሆን ብሎ ታጣቂዎቹ በዩንብርስቲው ግቢ ገብተው የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎችን እንዲደበድቡ አድርጎል። በዚህም የትግራይ ተወላጆችን ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በማጋጨት የስልጣን እድሜውን ለማራዘም የሚጠቀምበት ሴራ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

እንደትላንት ሁሉ ኢሕአፓ ወክንድ ይህን ተራ የወያኔ ተንኮል ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ወጣቱ ነቅቶ እንዲያከሽፈው አበክሮ ይጠቁማል። በዚሁ የወያኔ ተንኮል መነሻነት አስር የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃንም ኢሕአፓ ወክንድ አጥብቆ ያወግዛል። የገንጣዮች ማርከሻው ኢትዮጵያዊ አንድነት ነውና በማናቸውም አካል የሚቃጣብንን ማነቆና ሴራ በጣጥሰን ወጣቶች ሁሉ በጋራ ሁለገብ ጸረ ወያኔ ትግላችንን በማፋፋም ሕዝባችንን እና አገራችንን ነጻ እናውጣ።

**ሁለገብ  ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!! እናቸንፋለን!!**


*Joineprpyl@gmail.com* *Phone: 240-593-5390/202-677-1024*

*youtube.com/user/Ethiorevolution* *www.facebook.com/eprpyl*